# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
# የኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ
# ምክር ቤት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ
# አዋጅ ቁጥር 73

ሐምሌ 1994
ባህር ዳር

የኤች አይቪ ኤድስ ወረርሽኝ በመላው ዓለም በተለይም በታዳጊ አገሮች በከፍተኛ ሁኔታ በመስፋፋት በርካታ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ሥነልቦናዊ ችግሮችን ከማስከተል አልፎ በአሁኑ ወቅት የጤና ችግር ብቻ ሣይሆን የልማት ችግር በመሆን ህልውናቸውን በመፈታተን ላይ የሚገኝ በሽታ በመሆኑ፤

አገራችን ኢትዮጵያም የኤድስ ሥርጭት በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቶ ከሚገኝባቸውና በግንባር ቀደምነት ከሚጠቀሱት ታዳጊ አገሮች አንዷ ሆና ከመገኘቷም በላይ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በርካታ ዜጎቻችን ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ በመረጋገጡ፤

አያሌ የክልላችን ኗሪዎችም የዚሁ ሰለባዎች መሆናቸው በመታወቁ፤
በብሔራዊ ክልላችን ውስጥ እስካሁን ድረስ ሥርጭቱን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተለያዩ እንቅስቃሴዎች የተደረጉ ቢሆንም እነዚህ ጥረቶች የተበታተኑና ቅንጅታዊ አሠራር የጎደላቸው ከመሆኑ የተነሣ ከችግሩ ስፋትና አሳሳቢነት አንፃር በዚህ አካሄድ የሚደረገው እንቅስቃሴ ብቻ አመርቂ ውጤት ሊያመጣ ባለመቻሉ፤

የችግሩን ግዝፈት አስቀድሞ የተረዳው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት በነሐሴ ወር 1990 ዓም የአገሪቱ የጤና ፖሊሲ ክፍልና አካል የሆነ አገር አቀፍ የኤድስ ፖሊሲ ያወጣና ይህንኑ ፖሊሲ መሠረት በማድረግ ብሔራዊ የኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት የተቋቋመ በመሆኑ፤

በዚሁ ፖሊሲ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 10/2/ ሥር ችግሩን ለመቅረፍና ለማስወገድ መንግታዊና መንግሥታዊ የልሆኑ አካላትን ድርጅቶችንና የኅብረተሰብ ክፍሎችን ጥረት ማስተባበርና ቅንጅታዊ አሠራር ማጎልበት እንደሚገባ የተደነገገ በመሆኑ፤

ቀደም ሲል በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 17/1993 ተቋቁሞ የነበረውን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት አደረጃጀት ከአዲሱ የመንግሥት አወቃቀርና አደረጃጀት ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሐራዊ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት በ1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3.1 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤች አይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ------1994 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ተርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ እዋጅ ውስጥ፡-

1. " መከላከል" ማለት የበሽታው መንስዔ ተሕዋስ ማለትም ኤች አይ ቪ ወደ ጤነኛው ኅብረተሰብ ክፍል እንዳይተላለፍ ማድረግ ነው፡፡

2. " መቆጣጠር " ማለት /የኤች አይቪ/ ኤድስ ሥርጭት የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚወሰድ ክትትልና እርምጃ ነው፡፡ ይህም ለተደራቢ በሽታዎች / Opportunistic infections / በሚሰጠው ሕክምና፣ የሥነ ልቦና ምክር አገልግሎትና የቤት ውስጥ እንክብካቤ ሕሙማንን በማገዝ ቫይረሱን ወደ ጤነኛው የሕብረተሰብ ክፍል እንዳያስተላልፉ ኃላፊነት ለማሳደር የሚደረገውን ጥረትም ያካትታል፡፡

## 3. የኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት ስለመቋቋሙ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት ከዚህ በኋላ " ም/ቤቱ " እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2. ም/ቤቱ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሚዋቀሩ የየደረጃው ም/ቤቶች ይኖሩታል፡፡

## 4. ስለምክር ቤቱ መደበኛ አድራሻ

የምክር ቤቱ መደበኛ አድራሻ ባህር ዳር ነው፡፡

## 5. ዓላማዎች

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. ኤድስን የመከላከል እንቅስቃሴ በተቀናጀና በተባበረ አሠራር ላይ ተመስርቶና ተጠናክሮ እንዲካሄድ በማድረግ የክልሉ ሕብረተሰብ እራሱን ከወረርሽኙ እንዲጠበቅና ለኤድስ በሽታ እንዳይጋለጥ በመከላከል ለቀጣይ የዕድገት ጉዞው አስተማማኝ መሠረት መጣል፤

2. በኤድስ ሣቢያ በክልሉ ውስጥ እየደረሰ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነልቦናዊ ተጽእኖ ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ፤

## 6. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአገሪቱ የኤች አይቪ ኤድስ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ በተቀናጀ መንገድ ይተገበር ዘንድ ሁለንተናዊ ደጋፍ መስጠት፤

2. ብሔራዊ የኤች አይ ቪ ኤድስ ፖሊሲ ከአጠቃላዩ የጤና ፖሊሲ ጋር ተጣጥሞ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ የሚሆንበትን ተስማሚ ስልት መቀየስ፤

3. በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ተገቢውን ሥልጠናና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

4. የኤድስ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በየደረጃው የሚገኙ አካላት ሁሉ ለችግሩ ይበልጥ ቀዳሚ ትኩረት ሰጥተው የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማጎልበት ይቻል ዘንድ የተሟላ ተሳትፎና ድጋፍ በማሰባሰብ እንዲንቀሳቀሱ ማበረታታት፣ መቀስቀስ፤

5. በክልል ደረጃ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ይበልጥ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ እስከ አሁን ድረስ የሚከናወኑት የተናጠል ጥረቶች በተባበረና በተቀናጀ መልክ እንዲካሄዱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤

6. ለችግሩ መታደጊያ የሚሆን እርዳታና ድጋፍ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በተጠናከረ መንገድ እንዲሰበሰብ እና በአግባቡ በተግባር ላይ እንዲውል አመራር መስጠት እና አፈፃፀሙን መከታተል፤

7. የበሽታውን ሥርጭት በየጊዜው ለመከታተል ፣ ለመገምገምና የወደፊት እቅድና ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚያስችል ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ ማበረታታትና በዚሁ ሥራ ለሚሠማሩት ተፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፤

8. ለኤድስ በሽታ የማያጋልጥ የተሟላ ግንዛቤ እና ጤናማ ሰብአዊ ባህሪ እንዲጎለብት የክልሉን ህብረተሰብ በልዩ ልዩ ዘዴዎች መቀስቀስ፣

9. ሴቶች፣ ወጣቶች እና ሌሎች ለበሽታው በይበልጥ የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች እራሳቸውን ከበሽታው ለመከላከል ይቻላቸው ዘንድ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፤

10. በኤድስ በሽታ አስቀድመው የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች የጤና እንክብካቤ፣ የሥነ ልቦና፣ የምክርና እንደሁኔታው የማቴሪያል ድጋፍ የሚያኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

11. ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ የክልላችን ኗዋሪዎች፣ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ ሕፃናት፣ ታዳጊ ወጣቶችና ቤተሰቦቻቸው ሰብአዊ መብታቸው የተከበረ እንዲሆን ማድረግና ይኸው በሌሎች መጠበቁን ማረጋገጥ።

# ክፍል ሁለት
# ስለ ምክር ቤቱ አደረጃጀት

## 7. የምክር ቤቱ የሥልጣን አካላት

ምክር ቤቱ በክልል ደረጃ የሚከተሉት አበይት የሥልጣን አካላት ይኖሩታል፡-

1. ጠቅላላ ጉባዔ
2. የሥራ አመራር ቦርድ
3. ሴክሬታሪያት

# ንዑስ ክፍል አንድ
# ስለ ጠቅላላ ጉባዔ አባልነት

## 8. በአባልነት ለመመዝገብ ስለሚያበቁ ሁኔታዎች

1. ጠቅላላ ጉባዔው የምክር ቤቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሲሆን፣ በተቋም ሆነ በግል ደረጃ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልተው የተገኙ ሁሉ በዚህ አዋጅ መሠረት የጉባዔው አባላት ሆነው ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

ሀ. በክልላችን ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል የተሻለ አስተዋጽኦ ያላቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶችንና ሃይማኖታዊ ተቋማትን በበላይነት የሚመሩ ኃላፊዎች፤

ለ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን ሰብአዊ መብቶች ለማስከበርና ሌሎች ቫይረሱ የሌለባቸው ወገኖች እንዳይያዙ አስፈላጊውን የመከላከል ሥራ ለመሥራት የተደራጁ እና በእንቅስቃሴአቸው አመርቂነትም በምክር ቤቱ የሥራ አመራር ቦርድና በሴክሬታሪያት የተመሰከረላቸው  የማህበራት መሪዎች፤

ሐ. በክልል ውስጥ በግላቸው ከፍተኛ የበጎ አድራጎት እንቅስቃሴ በማድረግ የተሻለ አስተዋጽኦ ያላቸውና በተለይም ኤድስ የሚያደርሰውን አስከፊ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የጤና ችግር በሚገባ በማጤን በዚህ ዘርፍ ግዴታቸውን ለመወጣት ዝግጁዎች የሆኑ የምርምርና ማሰልጠኛ ተቋማት መሪዎች፣ ክበባት ማህበራትና ታዋቂ ግለሰቦች፤

መ. ትርጉም ያለው የማኅበረሰብ ጥቅም ለማስከበር የተቋቋሙ የሙያ፣ የጾታና የዕድሜ መሠረት ያላቸው የብዙሃንና የልማት ማህበራት መሪዎች፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው የአባልነት ጥያቄ አግባብ ያለውን ተቋም ወይም ማህበር የሥራ ኃላፊነት ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሁኔታው የሚወሰን ይሆናል፡፡

3. ማናቸውም የአባልነት ጥያቄ በሴክሬታሪያቱ በኩል ከቀረበ በኋላ በሥራ አመራር ቦርዱ ተገምግሞ ለጠቅላላ ጉባዔው ቀርቦ የሚወሰን ይሆናል፡፡

4. የጉባዔውን አባላት ብዛት፣ ማንነት፣ መብትና ግዴታ አፈፃፀም አስመልክቶ አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 9. የጠቅላላ ጉባዔው ሥልጣንና ተግባር

የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአገሪቱ የኤች አይ ቪ ኤድስ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣

2. በሥራ አመራር ቦርድ የሚቀርብለትን አመታዊ የሥራ እቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል፤

3. ለሥራ አመራር ቦርዱ አጠቃላይ የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

4. የሴክሬታሪያቱን ወቅታዊ የሥራ እንቅስቃሴና የኦዲት ሪፖርት ያዳምጣል፣ ውሣኔዎችን ያሳልፋል፤

5. የገቢ ምንጮች የሚገኙበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ ስለአፈፃፀሙም የሥራ አመራር ቦርዱ ክትትል እንዲያደርግ ተገቢውን መመሪያ ይሰጣል፤

6. የሥራ አመራር ቦርዱ በሚያቀርብለት አስተያየት መሠረት የአባልነት ጥያቄዎችን ተቀብሎ ይመረምራል፣ ያፀድቃል፣ እንደአስፈላጊነቱም ከአባልነት ይሠረዛል፤

7. ሰብሳቢውን ጨምሮ የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል፤

8. ምክር ቤቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም የሚወጡ እቅዶች፣መመሪያዎችና ስልቶች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

9. ዓላማዎቹን ሊያሳኩ የሚችሉ ሌሎች ሕጋውያን ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 10. ስለ ጠቅላላ ጉባዔው አመራር፣ ስብሰባና የአሠራር ሥነሥርዓት

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የምክር ቤቱ የበላይ ጠባቂ በመሆን ጠቅላላ ጉባዔውን ይመራል፡፡

2. የሴክሬታሪያት ኃላፊው የጠቅላላ ጉባዔው ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል፡፡

3. ጠቅላላ ጉባዔው በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤ እንደአስፈላጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊያደርግ ይችላል፡፡

4. ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት ውስጥ ሁለት ሦስተኛው የተገኙ እንደሆነ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

5. ማናቸውም የጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ ባስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት የአብላጫ ድምፅ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል ሆኖ ከተገኘ ሰብሳቢው የደገፈው ወገን የጉባዔው ውሣኔ ይሆናል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1-5 የሠፈረው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው የራሱን ስብሰባና የአሠራር ሥርዓት የሚመለከቱ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 11. የጠቅላላ ጉባዔው ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

የጠቅላላ ጉባዔው ሰብሳቢ የምክር ቤቱ የበላይ ጠባቂ ሲሆን በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የምክር ቤቱን ጉባዔ ጠቅላላ መደበኛና አስቸኳይ ሰብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል፤

2. የሥራ አመራር ቦርዱን እንቅስቃሴ በቅርብ ይከታተላል፣ መመሪያዎችን ይሰጣል፤

3. የሴክሬታሪያቱን ኃላፊ ይሾማል፣ ይሽራል፤

4. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለምክር ቤቱ አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪ ያቀርባል፤

5. በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፤

6. የጠቅላላ ጉባዔው አባላትና የበጎ ፈቃድ ደጋፊዎች እንዲበራከቱ ያበረታታል፤

7. በአች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ዙሪያ በሚደረጉ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፍ ሲጋበዝ ይገኛል፣ ወይም ሌሎች እንዲገኙ ይወክላል፤

8. በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ዙሪያ አመርቂ ተግባራት ላከናወኑ በተቋማትና ግለሰቦች በጠቅላላ ጉባዔው ውሣኔ መሠረት የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፤

9. የምክር ቤቱ ገንዘብና ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

10. አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነ ጊዜ የምክር ቤቱን የሂሣብ መዛግብት በታወቁ የሂሣብ ባለሙያዎች እንዲመረመሩ ያደርጋል።

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ስለ ሥራ አመራር ቦርድ

### 12. ስለ ቦርዱ አሰያየም፣ ስብሰባና የአሠራር ሥነሥርዓት

1. ምክር ቤቱ በጠቅላላ ጉባዔው ምርጫ የሚሰየም የራሱ የሥራ አመራር ቦርድ ይኖረዋል፤ የቦርዱ አባላት ቁጥርና ተዋጽኦ እንደአስፈላጊነቱ በምክር ቤቱ የሚወሰን ይሆናል።

2. የቦርዱ ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባዔው ይሆናል።

3. ቦርዱ ከአባላቱ መካከል የሚመረጥ ሰብሳቢ ሲኖረው የሴክሬታሪያቱ ኃላፊ የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል

4. የሥራ አመራር ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ እንደአስፈላጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያደርጋል።

5. ከቦርዱ አባላት ውስጥ ሁለት ሦስተኛው በስብሰባ ላይ የተገኙ እንደሆነ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል።

6. ማናቸውም ጉዳይ በስብሰባ ላይ በተገኙት አባላት የአብላጫ ድምፅ ከተደገፈ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ወገን የቦርዱ ውሣኔ ይሆናል።

7. ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ 1-6 የሠፈረው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባና የአሠራር ሥነ ሥርዓት መመሪያዎችን አውጥቶ በሥራ ላይ ሊያውል ይችላል።

13. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

የሥራ አመራር ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የምክር ቤቱ ሥራ አስፈፃሚ አካል በመሆን ይሠራል፤

2. ከለጋሽ ግለሰቦች ፣ ከመንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ፣ ከሃይማኖትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ቅርብና የጠበቀ የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፤

3. የኤች አይ ቪ ኤድስን በሽታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ታዋቂ ግለሰቦች እንቅስቃሴ ያስተባብራል፣ በመካከላቸውም የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

4. በሴክሬትሪያቱ ተዘጋጅቶ የቀረበለትን ዓመታዊ የሥራ እቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ ገምግሞ ከአስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባዔው በማቅረብ ያስፀድቃል፤

5. በበጀት ውስጥ ያልተመለከተ ገቢ ሲገኝ በሥራ ላይ በማዋል ጠቅላላ ጉባዔው ሲሰበሰብ በጀቱን ያፀድቃል፤

6. የሴክሬታሪያቱን እጩ /ኃላፊ ገምግሞ/ ለጠቅላላ ጉባዔው ሰብሳቢ በማቅረብ ያሾማል፤

7. ለምክር ቤት አባልነት የሚቀርቡ ጥያቄዎችንም ወይም በዚሁ ምክር ቤት ውስጥ በአባልነት ሊመዘገቡ የሚገባቸውን አስፈለጊ ተቋማት እና ማኅበራት በሚመለከት የሚነሱ ጉዳዮችን በመገምገም ከአስተያየት ጋር ለምክር ቤቱ የበላይ ጠባቂ ያቀርባል፤

8. በጠቅላላው ጉባዔ የሚተላለፉትን ውሣኔዎችንና የሚሰጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤

9. በመደበኛ ስብሰባዎቹ ወቅት ለጠቅላላ ጉባዔው ስለአከናወናቸው ተግባራት ሪፖርት ያቀርባል፤

10. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ዙሪያ በክልሉና አገር አቀፍ ደረጃ ከሚንቀሳቀሱ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር የጠነከረ ግንኙነትና ትብበር እንዲኖር ያደርጋል፤

11. ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል በሚደረጉ አገር አቀፋዊ፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ስብሰባዎች ይካፈላል፤

12. አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ አጋዥ የሆኑ አደረጃጀቶችን ያቋቁማል፤

13. ለሴክሬታሪያቱ የሚቀርቡትን ፕሮጀክቶች ይገመግማል፣ ያፀድቃል፤

14. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1፣3፣8፣10 ሥር የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደአስፈላጊነቱ ለሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢውም በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ስለ ምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት

### 14. አደረጃጀትና ተጠሪነት

1. የምክር ቤቱን የዕለት ከዕለት ሥራዎች የሚያከናውን ሴክሬታሪያት የምክር ቤቱ አንዱ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ተቋቁሟል፡፡

2. ሴክሬታሪያቱ በአንድ የበላይ ኃላፊ የሚመራ ሲሆን በዋናው ጽሕፈት ቤትና በተዋረድ አካላቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

3. የክልሉ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት መደበኛ አድራሻ በክልሉ ርዕሰ ከተማ ይሆናል፡፡

4. ሴክሬታሪያቱ ተጠሪነቱ ለቦርዱና ለርዕሰ መስተዳድሩ ሲሆን በእነርሱም በኩል ለምክር ቤቱና ለክልል መስተዳድሩ ምክር ቤት ይሆናል፡፡

5. ሴክሬታሪያቱ ምክር ቤቱን ወክሎ ይከሳል፣ ይከሰሳል፡፡

### 15. የሴክሬታሪያቱ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 እና 13 ለጠቅላላ ጉባዔው እና ለሥራ አመራር ቦርዱ የተሰጧቸው አጠቃላይ ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ሴክሬታሪያቱ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. በምክር ቤቱ ውሣኔዎችና የሥራ ፕሮግራሞች ላይ በመመሠረት የኤድስ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልሉ የሚደረጉትን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎች በበላይነት ያስተባብራል፣ ለተግባራዊነታቸውም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

2. ምክር ቤቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፤

3. ኤች አይ ቪ ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ የጠቅላላ ጉባዔው አባላት፣ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ ግለሰቦችና ድርጅቶችን

እንቅስቃሴ ያስተባብራል፣ በመካከላቸው የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ በቅርብ ይከታተላል፤

4. የክልሉ ኅብረተሰብ ስለ ኤድስ እና ችግሮቹ ግንዛቤ እንዲኖረው ክልላዊና አገር አቀፍ ስብሰባዎችና ዓውደ ጥናቶችን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁም ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

5. የኤች አይ ቪ ኤድስን በሽታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ታዋቂ ግለሰቦችን ጥረት ያስተባብራል፣ የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

6. በክልሉ የኤች አይ ቪ ኤድስ ገፀታ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ እንደአስፈላጊነቱም ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያስተላልፋል፤

7. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የዞን ቅርንጫፍ ሴክሬታሪያት ተወካዮችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፤

8. ለሥራው መቃናት የሚያግዙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ያደራጃል፣ ሥራዎቻቸውንም በቅርብ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

9. በሥሩ የተቋቋሙትን ንዑሳን ኮሚቴዎች ሰብሳቢና ፀሐፊ ይሰይማል፤

10. የአጭር የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የሥራ እቅድና በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ በእርሱም አማካኝነት ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በአግባቡ በተግባር ላይ ያውላል፤

11. የጠቅላላ ጉባዔውንና የሥራ አመራር ቦርዱን ውሣኔዎች ለክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት ያስተላልፋል፣ በወቅቱ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

12. ከተለያዩ ለጋሾች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፤

13. የሥራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ ለቦርዱ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፣ በየግማሽ አመቱ ደግሞ ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፤

14. ጥናትና ምርምር ሥራዎች ድጋፍ ይሰጣል፣ ያበረታታል፤

15. በምክር ቤቱ የበላይ ጠባቂ፣ በጠቅላላ ጉባዔውና በሥራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

16. ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል በሚደረጉ አገር አቀፋዊ፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ስብሰባዎች ይካፈላል፤

# ክፍል ሦስት
# ስለምክር ቤቱ የተዋረድ እርከኖች
# አደረጃጀትና ሥልጣን

## 16. ዞን አቀፍ አደረጃጀት

ምክር ቤቱ በዞን ደረጃ የሚዋቀር ሆኖ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. ጠቅላላ ጉባዔ
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ
3. የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ሥራዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

## 17. ስለ ዞን ጉባዔ አመራር

የዞን ጠቅላላ ጉባዔ በሚመለከተው ዞን ዋና አስተዳዳሪ ይመራል፣ ይሰበሰባል፡፡

## 18. ስለ ዞን የሥራ አመራር ኮሚቴ አሰያየም

የዞን የሥራ አመራር ኮሚቴ በዞን ጉባዔ ተመርጦ የሚሰየም የዞን ም/ቤት አስፈፃሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለዞን ጉባዔ ይሆናል፡፡

## 19. ስለ ዞን የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ሥራዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

የዞን የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ሥራዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በክልሉ ሴክሬታሪያትና በሚመለከተው የዞን አስተዳደር በሚደረግ መመካከር የሚቀጠር አንድ የበላይ ኃላፊ የሚመራ ሲሆን የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴው ለዞን ጉባዔ ሰብሳቢና በክልል ደረጃ ለተቋቋመው ም/ቤት ሴክሬታሪያት ይሆናል፡፡

## 20. በተዛማጅ ድንጋጌዎች ስለመሥራት

በዞን ደረጃ ይህንን አዋጅ መሠረት አድርገው የተቋቋሙ የዞን ጉባዔ የሥራ አመራር ኮሚቴና የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ሥራዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በየተደራጁባቸው ዞኖች ውስጥ እንደአግባብነቱ ለሥራቸው ባስፈለጋቸው መጠን በክልል ደረጃ የተቋቋሙትን የምክር ቤቱን ጠቅላላ ጉባዔ፣ የሥራ አመራር ቦርድና የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት አስመልክቶ በዚህ አዋጅ በክፍል ሁለት ሥር የሰፈሩትን ድንጋጌዎች ሊሠሩባቸው ይችላሉ፡፡

## 21. ወረዳ አቀፍ አደረጃጀትና ሥልጣን

ምክር ቤቱ በወረዳ ደረጃ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. ጠቅላላ ጉባዔ
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ
3. ቅርንጫፍ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

## 22. ስለ ወረዳ ጠቅላላ ጉባዔ ተዋጽኦ፣ ኃላፊነትና አመራር

በወረዳ ደረጃ የሚቋቋም ጠቅላላ ጉባዔ በሚመለከተው ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ የሚመራ ሲሆን አባላቱን፣ ሥልጣንና ተግባሩን፣ የስብሰባ ጊዜውንና የአሠራር ሥነ ሥርዓቱን አስመልክቶ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 8 - 11 በሰፈሩት ድንጋጌዎች መሠረት አስፈላጊነታቸው እየታየ በሥራ ላይ የሚውሉ ይሆናሉ፡፡

## 23. ስለ ወረዳ ሥራ አመራር ኮሚቴ አሰያየም፣ ኃላፊነትና ተጠሪነት

የወረዳ ሥራ አመራር ኮሚቴ በወረዳ ጠቅላላ ጉባዔ የሚሰየምና ተጠሪነቱም ለዚሁ ጉባዔና በክልል ደረጃ ለተቋቋመው ሴክሬታሪያት የሆነ አስፈፃሚ አካል ሲሆን አሰያየሙን ሥልጣንና ኃላፊነቱን እንዲሁም የስብሰባና የአሠራር ሥነ ሥርዓቱን በሚመለከት ክልል አቀፉን የሥራ አመራር ቦርድ አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 እና 13 ሥር የሰፈሩት ድንጋጌዎች አግባብነታቸው እየታዩ በተመሣሣይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

## 24. ወረዳ አቀፍ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ሥራዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

1. የወረዳ ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ሥራዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለወረዳው ሥራ አመራር ኮሚቴ፣ ለጠቅላላው ጉባዔና በእርሱም አማካኝት ለክልሉ ሴክሬታሪያት ሆኖ ዝርዝር ሥልጣንና ኃላፊነቱን በተመለከተ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 ሥር የክልሉን ሴክሬታሪያት ሥልጣንና ተግባራት አስመልክቶ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው እየታዩ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፤
2. ጽ/ቤቱ በክልሉ ሴክሬታሪያትና በሚመለከተው የወረዳ አካል ጋር በሚደረግ መመካከር በሚቀጠር አንድ የወረዳ የኤድስ አስተባባሪ ይመራል ይተዳደራል፡፡

## 25. ቀበሌ አቀፍ አደረጃጀት

ምክር ቤቱ በቀበሌ ደረጃ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. ጠቅላላ ጉባዔ
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ
3. የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

## 26. ስለ ጠቅላላ ጉባዔው አወቃቀር፣ ተዋጽኦ፣ የሥራ ኃላፊነት፣ አመራር፣ የስብሰባ ጊዜና የአሠራር ሥነ ሥርዓት

የቀበሌው ጠቅላላ ጉባዔ በቀበሌው አስተዳደሪ የሚመራ ሆኖ አወቃቀሩን፣ የአባልነት መቀበያ መስፈርቶችን፣ የሥራ ኃላፊነቱን፣ የስብሰባ ጊዜውን የአሠራር ሥነ ሥርዓቱንና የመሣሰሉትን በተመለከተ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 8-11 ሥር የክልሉን ጠቅላላ ጉባዔና የሰብሳቢውን ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ የስፈሩት ዝርዝር ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው እየታዩ በቀበሌ ደረጃ ለሚከናወነው የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ሥራ ባስፈለገ መጠን በተመሣሣይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

## 27. ስለ ቀበሌ ሥራ አመራር ኮሚቴ

የቀበሊ ሥራ አመራር ኮሚቴ ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየም የበታች አስፈፃሚ አካል ሲሆን ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቱን በሚመለከት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 እና 13 ሥር በክልል ደረጃ ለተቋቋመው የሥራ አመራር ቦርድ የተፃፉት ድንጋጌዎች ለሥራው ባሰፈለገ መጠን በተመሣሣይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

## 28. ስለ ቀበሌ ፀረ ኤድስ ሥራዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

በቀበሌ ደረጃ የተሰየመው ሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ የራሱ ጽ/ቤት የሚኖረው ሲሆን ይኸውም የቀበሌው ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጭምር ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 29. የማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

የቀበሌ ፀረ ኤድስ እንቅስቃሴዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ከሥራ አመራር ኮሚቴው አባላት መካከል በሚመረጥ አንድ የፀረ- ኤድስ አስተባባሪ የሚመራ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 ሥር የክልሉን ሴክሬታሪያት ሥልጣንና ተግባር አስመልክቶ በተጻፉትና አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች የተወሰነ ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 30. ስለምክር ቤቱ የገቢ ምንጭ

የምክር ቤቱ የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ አበዳሪ ተቋማት በጐ አድራጊ ግለሰቦች የሚገኝ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ፤
2. ከክልሉ መንግሥት የሚገኝ ድጋፍ፤

## 31. ስለ ምክር ቤቱ የበጀት ዓመት

የምክር ቤቱ የበጀት ዓመት የክልሉ መንግሥት የሚሠራበት የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

## 32. ስለበጀት አስተዳደርና ሂሣብ አያያዝ

1. ምክር ቤቱ በክልሉ ሴክሬታሪያት ስም የራሱን ተንቀሳቃሽ የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፡፡
2. ምክር በቱ የራሱ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩም አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይገለፃል፡፡
3. የምክር ቤቱ ሂሣብ በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ በገለልተኛ ኦዲተሮች እንዲመረመር ይደረጋል፡፡

## 33. ስለምክር ቤቱ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ሃብቶች

ምክር ቤቱ በየደረጃው ባሉት አካላቱ በኩል ውል ሊዋዋልና የንብረት ባለቤት ሊሆን ይችላል፡፡

## 34. የተሻሩ ሕጎች

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤትን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባርን ለመወሰን የወጣው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 17/1993 ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

2. የኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራትን አስመልክቶ እስከ አሁን ድረስ በክልሉ ውስጥ ፀንቶ የሚሠራበት ማናቸውም መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ ሆኖ ከተገኘ ይህንን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 35. አዋጁን ስለማሻሻል

ይህን አዋጅ እንዲሻሻል የክልሉ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባዔ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የወሰነ እንደሆነ ህግ በሚፈቅደው መሠረት ለብሔራዊ ክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 36. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደምቦችን የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቦርዱ ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደምቦች ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 37. የመተባበር ግዴታ

1. ማንኛውም ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ለተጠቀሰው ዓላማ አፈፃፀም ስኬታማነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተገለፀው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም የክልሉ መንግሥታዊ መ/ቤት ወይም ድርጅት ከመደበኛ ተግባርና ኃላፊነቶቹ ጐን ለጐን ኤች. አይ. ቪ. ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራዎችን አጣምሮ እንዲያከናውን ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡

## 38. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ታይቶ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር
ሚያዝያ --------------------------ቀን 1994 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት